 

# አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሀለሁ እልል እልል(፪)
ለአለም አለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድኃኒአለም(፪)

ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ

አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አዉቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ

ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ስጦታ
በቀንም በለትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ እጹብ ለአንተ ሥራ

አምላክ ሆይ ምስጋናለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ደኃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎል እንደገና

አድርገህልኛልና በቸርነትህ
አመሰግንሀለሁ እልል እልል(፪)
ለአለም አለም አማኑኤል
እገዛልሃለሁ መድኃኒአለም(፪)

 

## ተክለሃይማኖት ተወለዱ

ተክለሃይማኖት ተወለዱ እሰይ (፪)
የአለም ብርሃን (፪) የጽድቅ ፀሐይ (፪)
ባለሟል ለአምላክ አዶናይ

## ገብርኤል መልአክ

ገብርኤል መልአክ መጽአ
ወዜነዋ (፬) ለማርያም (፪)
በዕንቁ ባሕርይ (፪) እንዘ ትፈትል ወርቀ (፪)

ትርጉም :-
መልአኩ ገብርኤል መጥቶ ለእመቤታችን
ለማርያም ወርቅና ሐር እያስማማች
ስትፈትል አስረድቶ ነገራት